4.2.7. **የመፀዳጃ ቤት ሁኔታ**

4.2.7.1. የመፀዳጃ ቤት ክፍል ጣሪያ ከፍታ ቢያንስ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) ሊሆን ይገባል፤

4.2.7.2. የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 1.2 ሜትርበ1.2 ሜትር የሆነ መሆን አለበት

4.2.7.3. ለ20 (ሃያ) ወንበር ወይም ተገልጋይ አንድ የመፀዳጃ መቀመጫ ለወንድናለሴት የተለየ ሊኖር ይገባል፤

4.2.7.4. አንድ የሽንት መሽኒያ (ዩሪናል) ለ20 (ሃያ) ወንበር ወይም ተገልጋይ ሊኖር ይገባል፤

4.2.8. **የሰራተኛ ገላ መታጠቢያ**

4.2.8.1. የገላ መታጠቢያ ክፍል ጣሪያ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) ከፍታ ቢያንስ ሊሆን ይገባል፤

4.2.8.2. የክፍሉ ስፋትቢያንስ 1.2 ሜትር*1.2 ሜትር (አንድ ነጥብ ሁለት ሜትር በአንድ ነጥብ ሁለት ሜትር) መሆን አለበት

4.2.8.3. የመታጠቢያ ክፍሉ ንጹህ አየር ማስገቢ ከኮረኒስ 20 ሴ.ሜ ዝቅ ብሎ በ45 ዲግሪ ወደታች ተከፋች የሆነ መስኮት መኖር አለበት

4.2.8.4. ለ20 ሰራተኛ በንፅፅር አንድ የወንድ አንድ የሴት ሻወር ሊኖር ይገባል፡፡

4.2.9. **የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ**

4.2.9.1. ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ (በስራ እንቅስቃሴ ከሚመነጭበት ቦታ) መሰብሰብ አለበት

4.2.9.2. የቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ማቆያ (garbage bin) ሶስት አራተኛው ሲሞላ ወደ ድርጅቱ አጠቃላይ መሰብሰቢያ መግልበጥ አለበት፡፡

4.2.10. **የድርጅቱ ሰራተኞች**

4.2.10.1. ድርጅቱ በስሩ የሚሰሩ ሰራተኞች በዚህ ደረጃ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች እና የአሰራር ቅደም ተከተሎች ላይ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ መሰልጠናቸውን ማረጋገጥ አለበት ፡፡

4.2.10.2. ማንኛውም ሰራተኛ ከምግብ ወለድ በሽታ ነጻ መሆን ስላለበት በአመት አራት ጊዜ/በየሶስት ወሩ/ የጤና ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4.2.10.3. ለሰራተኞችንጭ/ፈካ ያለ ሙሉ የስራ ልብስ ባለቅያሬ መኖር አለበት፡፡

## 5. የግሮሰሪ/መጠጥ ቤት

5.1. **የድርጅቱ አሰራር ዘይቤ**

5.1.1. የግሮሰሪ/መጠጥቤት የዕቃ አስተጣጠብ (Cleaning, sanitizing and dish washing) የአሰራር መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

5.1.2. የግሮሰሪ/መጠጥቤትየደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር መመሪ ሊኖረው ይገባል፡፡

5.1.3. የግሮሰሪ/መጠጥ ቤት የእጅ አስተጣጠብ እና የግል ንፅህና የአሰራር መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

5.1.4. የግሮሰሪ/መጠጥ ቤትየተበላሹ መጠጦችና ዕቃዎች አወጋገድ የአሰራር መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD



©ESA

6.9. ኮርኒስ ለማፅዳት የሚያመች፣ ፈካ ያለ/ነጭ ቀለም የተቀባ ያልተከፈተ/ያልተቀደደ፣ ሙቀትን መቋቋም ከሚችል ደረጃውን ከጠበቀ የግንባታ ቁሳቁሶች የተሰራ መሆን አለበት (ከስላብ፣ ማይካ/ኢፖክሲ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ የግንባታ ቁሳቁስ)፡፡

## 7. የአገልገሎትተጠቃሚዎችማስተናገጃክፍል

7.1. የክፍሉ ሁኔታ፡-ወለል፣ ግድግዳና ኮርኒስ በአንቀጽ በ6.3፣6.7፣6.8፣እና 6.9 የተገለፀውን መስፈርት ማሟላት አለበት

7.2. ያልተሰነጣጠቀ፣ ከቆሻሻ የፀዳ፣ የቧንቧና ፍሳሽ መስመሮች እንጥብጣቢና ፍሳሽ የሌለው፤ ሊፀዳና ሊታጠብ በሚችል ሁኔታ ፈካ ያለ ቀለም የተቀባና በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡

7.3. ከማንኛውም ዓይነት ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ቆርጣሚ እንስሳትና ሌሎች ነፍሳት የፀዳ መሆን አለበት፡፡

## 8. የመጠጦች ማስቀመጫ ክፍል/መጋዘን

8.1. የክፍሉ ሁኔታ፡-ወለል፣ ግድግዳና ኮርኒስ በአንቀጽ በ6.3፣6.7፣6.8፣እና 6.9 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት አለበት

8.2. የመጋዘኑ አሰራር ሙቀትን መቆጣጠር በሚችል ሁኔታና ለቆርጣሚ እንስሳት እና ለተለያዩ ነፍሳት ያልተጋለጠ መሆን አለበት

8.3. ከደረቅና ከፍሳሽ ቆሻሻ የፀዳ መሆን አለበት

8.4. በቂ የአየር ዝውውርና የብርሃን መጠን ያለው መሆን አለበት፡፡

8.5. የመጠጦች ዝርዝር እና የገቡበት ቀን ተመዝግቦ መቀመጠ ያለበት ሲሆን፤ እንዲሁም ዝርዝሮች የተለጠፈና መጀመሪያ የገባው መጀመሪያ መውጣት አለበት፡፡

8.6. ክዳን ያለው በቀላሉ ሊታጠብና ሊጸዳ የሚችል በእግር የሚከፈትና የሚዘጋ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሊኖር ይገባል፡፡

## 9. የመገልገያ ዕቃዎች ዝግጅትና የንጽህና የአያያዝ

9.1. እያንዳንዱ የግሮሰሪ/መጠጥ ትልቁ ማቀዝቀዣ ወይም ዲፕ ሪፍሬጀሬተር ሊኖረዉ ይገባል፡፡

DRAFTE ETHIOPIAN STANDARD



©ESA

